# የድህረ ገፅ ደንብ ! ! !

## የድህረ ገፅ ስያሜ:- ፀ ጋ ዬ

1. ዓላማ
2. ተግባር
3. መረሐ ግብር
4. መምሪያዎች
5. ስያሜ
6. ዓርማ

## 1. ዓላማ፣

በጠቅላይ ሚኒስትር ሂሮድስ መለስ ዜናዊ የሚመራው ኅሳዊና ፋሽስታዊ አገዛዝን ግባተ መሬት ለማፋጠን በሚካሄደው ዲሞክራሲያዊ ትግል፣
- የግንዛቤን አድማስ በማስፋፋት የህሊናን መሰናዶ ለማሟላት፣
- የሕዝቡን ዲሞክራሲያዊ ትግል በህሳብ ለማገዝ፣
- እንዲሁም ሁለገብ የሆኑ ህገራዊ ጉዳዮችን በብዕር ለዛ ለመቃኘት ይሆናል።

በተጨማሪም የ 21ኛውን ምዕተ ዓመት ተረካቢ የሆኑ ልጆችን በሚመለከት በጣም በጥቂቱ የመክፈቻ መሠረት ለመጣል ( የቻለ አስፍቶ ሊቀጥል ይችላል፣ ማሳው ድንግል ነውና )፣

## 2. ተግባር፣

2.1 የድርሻችንን ለመወጣት ድልድይ መዘርጋት / መንገድ ለመክፈት /
2.2 የልምድ፣ የዕውቀት እና የተመክሮ ምክለት ለመፍጠር፣
2.3 የስደትን ሕይወት ለማናገር፣
2.4 የሰው ልጅ የነቃው የህሊና ክፍል በእህልና በመጠጥ ብቻ አይኖርም:: የሰው ልጅ የነቃው የህሊና ክፍል ትልቅ ውስብስብ ረቂቅ ምጥቅ ልዩ ማሳ ነው:: ማሳው ደግሞ በመስኖ መልማት አለበት:: መስኖው ደግሞ ጥበብ ነው:: ጥበብ ደግሞ ረቂቅ የሆነ ቅዱስ ፀጋዊ መንፈስ ነው:: ስለዚህ እኛ እና የጥበብ መንፈስን ጥበብን ወይንም ጥበብና እኛን በሰማንያ እንደአቅማችን ለማጋባት ነው::

## 3. መረሐ ግብር፣

እንደሚታወቀው መርሀ ግብር መሪ የተግባር ትልም ማለት ነው::
ለአንድ ድርጅት ወይንም ለግል ሕይወትም መርሀ ግብር ያስፈልገዋል:: መርሀ ግብር የሌለው አካል ዓይን የለውም:: ዓይን ካልኖረም ደግሞ የፈለገ ዓይነት ብቃት ቢኖረው አይደለም ሌላውን እራሱን እንኳን መምራት አይችልም::

መርሀ ግብር የተግባር ትልም፣ መሪ፣ አቅጣጫ አመልካች መንገድ ቀያሽ መሀንዲስ ነው:: ስለሆነም ድህረ ገጻችን ሦስት ደረጃ ( ምዕራፍ ) ያላቸው ትልሞች አሉት።

3.1 የአጭር ጊዜ _ ከአንድ ሳምንት እስከ አንድ ወር፣
3.2 የመካከለኛ ጊዜ _ ከአንድ ወር አስከ አንድ ዓመት፣
3.3 የረዥም ጊዜ _ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት፣

አሁን በአለን አቅምና ሁኔታ በአጭር ጊዜ መርሀ ግብራችን መንቀሳቀስ አንጀምራለን:: ማለትም በእጃችን ባሉ ነገሮች ዙሪያ መርሐ ግብራችን አኃዱ ይላል:: ቢያንስ ለእያንዳንዱ መምሪያ በወር አንድ ጽሑፍ ማውጣት የሚያስችል ሙሉ መሰናዶው ተጠናቋል::

## 4. መምሪያዎች፣

ቃና
ማዕዶት
አብረታት
የሎሬት ተስፋ
ዕድምታ

## 5. ስያሜ፣-

ፀጋዬ ድህረ ገፅ፣

## 6. ዓርማ፣-

በአለም ካርታ ውስጥ የአፍሪካ ካርታ፣ በአፍሪካ ካርታ ውስጥ የኢትዮጵያ ካርታ፣- በኢትዮጵያ ካርታ ውስጥ የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋ ገ/መድኅን ፎቶ፣

### 6.1 የዓርማ ትርጉም፣

. የዓለም ካርታ መዐቀፉ የሆነበት ምክንያት ጥበብ ድንበር፣ ወሰን የማይገድበው በመሆኑ፣
. ድህረ ገፃችን ዓለም አቀፋዊ ስለሆነ፣
. የሌሎች ሀገር ፅሑፎች፣ ግጥሞች ልናስተናግድ ሀሳቡ ስላለን ነው::

## የድህረ - ገፅ ቢጋር፣

1. የድህረ ገፁ ስያሜ፣ **ፀ ጋ ዬ**

2. ምልክት፣ ፀ፣ በአረንጋዴ
ጋ፣ በቢጫ
ዬ፣ በቀይ

# ሎሬት ፀጋዬ

3. አሰባሳቢ ወይንም መሪ መፈክር፣

**ትውልዳዊ - ድርሻችንን - እንወጣ**

## 4. ስለምን የድህረ ገፅ ስያሜ ፀጋዬ ተባለ ?

4.1 ብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን ታላቅ የሥነ ጥበብ ዘውድ በመሆኑ፣
4.2 በሰሞናተ ዕለተ ህልፈተ ወርሀ ላይ አዲስ የድህረ ገፅ ምሥረታ ፅንሰ ሀሳብ ስለፈለቀ፣
4.3 እንደ ዘመኑ ታዳሚነታችን ለፀሀፊ፣ ለደራሲ፣ ለገጣሚ፣ ለባለቅኔና ለተርጓሚው ክቡር ብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን ያለንን የማያብለውን፣ የማይማርተውን፣ የማይጠወልገውን ፍጹምና ልዩ ፍቅራቸውን ለማዘከር፣
4.4 ከሀገር ውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚኖሩ ታዳጊ ልጆችና ወጣቶች ታላቁን የጥበብ አባወራ ብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅንን እንደማተባቸው ተመልክተው ሳይዘናጉ በመንፈሳቸው ሁልጊዜ እንዲያስታውሱት ሲሆን፤ ማተብ ደግሞ ከሁሉም ዓይነት የቃል ኪዳን ቀለበት እና ውል በላይ የጠነከረ ነው::
4.5 በተለይ ለተዋሕዶ ልጆች ደግሞ የጥበብ አባታችን፣ መምህራችን የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን የብዕር ምርት፣ የመንፈስ ፀጋ፣ የመድኅኒዓለም ስጦታው ይዞታዊ ቀመር ከዕምነታችን ዶግማና ቀኖና ጋር በቅጡ የተዋሀደ ስለሆነ፣
4.6 ስሙ ከመቃብር በላይ ነውና ለስሙ፣ለሥራው፣ ለወርቁ ስጦታው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ <u>የድኅረ ገፅአችን ስያሜ ፀጋዬ</u> ተባለ::

## 5. ስለምን ዓርማው የአፍሪካ ካርታ ሆነ?

5.1 ኢትዮጵያ ሀገራችን በአፍሪካ አህጉር ስለምትገኝ፣
5.2 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መናህሪያ ኢትዮጵያ ስለሆነች፣
5.3 የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽን ጽ/ቤትም ማዕከልም ኢትዮጵያ በመሆኗ፣
5.4 የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ሊቅነት፣ ጠበብትነት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ በተለይም የጥቁሮች ኮከብ በመሆኑ፣
5.5 ብላቴን ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን የምርት ደረጃ ዕውቅና የአፍሪካ ባለቅኔ ገጣሚ ስለሚያሰኘው፣

## 6. ስለምን የዓለም ካርታ የዓርማው ማቀፊያ ሆነ?

6.1 የሥነ ፅሑፍ ቅዱስ መንፈስ ድንበር የለሽ በመሆኑ፣
6.2 የአንድ ሀገር ዲሞክራሲያዊ ትግል መንፈስ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዓለም አቀፋዊ ባህሪ ስላለው፣
6.3 ብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን የዓለምን የሥነ ጽሑፍ ደረጃም አሳድጎታል፣ በግጥም
6.4 የአፃፃፍ ህገ - ሥርዓት * የፀጋዬ ቤት* ልክ እንደ ሶኔትና እንደሌሎቹ አንድ የፈጠራ ልቅና እና ደረጃ ያለው ታላቅ ጉልላት በመሆኑ፣
6.5 ቋንቋችን እንደተፈጥሮአችን ለዬት ያለ ተፈጥሮአዊ ባህሪ ያለው ቢሆንም አማርኛ የሴማዊ ቤተሰብ አባል ነው:: ሴማዊነት ደግሞ ሁሉ አቀፍ የቋንቋ ሥረ ግንድ ነው። **ለምሳሌ:-** አረብኛ እና ሂብሩ ሴማዊ ናቸው:: አረብኛ ተናጋሪ ሀገሮችም ሆኑ ሂብሩ ቋንቋ ተናጋሪዎች የአለም ክፍለ አካል ናቸው::ስለዚህ አማርኛም በመወራረስ ይሁን በመሸጋሸግ የአካልነት ባህሪው ዓለም አቀፋዊነት አለው ዕምነት አለን::
6.5 ቋንቋ ሁልጊዜ ይዛመዳል / ኢንተግሬት / ያደርጋል:: ስለዚህ የእኛም ቋንቋችን ኢንተግሬት እንደሚያደርገው ሁሉ እኛም የሌሎችን ቋንቋ እንደ ብቃታችን ደረጃ ኢንተግሬት ማድረግ እንዲቻል ሁኔታዎችን የምናመቻች በመሆኑ፣ / ህረ ገፅአችን ባለንበት ሀገር ጀርመንኛ ከተቻለም በእንግሊዘኛ ፅሑፎችን ድህረ ገፅአችን ላይ ቤት ለእንግዳ እንላለን/::

## 7. ስለምን ከኢትዮጵያ ካርታ ውስጥ የሎሬት ፀጋዬ ምስል /ፎቶ/ ሊሆን ታሰበ ?

7.1 ድህረ ገፅአችን የሥነ ፅሑፍ ዐውድማ፣ አውደ ዕልፍኝ ነው:: ጋሽ ፀጋዬ ደግሞ የሥነ ፅሑፍ አባት ነው:: የሥነ ጥበብ ሥርዎ ግንድ ነው::

7.2 የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ፎቶ ( ምስል ) ከመቃብር በላይ የሆነና ዘመን የማይሽረው የህሊናችን ሀውልት ልዩ ማህተም ነው::

7.3 የእያንዳንዱ የጋሽ ፀጋዬ ምርት ዓውድማ በእያንዳንዱ የነቃው የህሊና ክፍል ውስጥ ዘመን የማይሽረው ወጀብ የማይነቀንቀው ዓውሎ ነፋስ የማያጠቃው ፅኑ አምደ - ሀውልት አለ:: እሱ ደግሞ የጋሼ ፀጋዬ የጥበብ ሰውነት መፈጠሪያ የሆነው ስነ ገፅ ምስሉ ወይንም ፎቶ ነው::

7.4 ተጨማሪ ተግባር ሁል ጊዜ በዓርማው ጎን ዕለተ ህልፈቱን በማሰብ የተደረገው ግጥም እና ቀጣዩ ክፍል የፎቶው ታዳሚ ይሆናል:: እንዲሁም የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ሥራዎችም ሆነ ሌሎች የጥበብ ሰዎች ስለ እርሱ የሚሠሯቸውን ሥራዎችም ይካተታሉ::

## 8. የድህረ ገፅ ቋሚ የመክፈቻ ስንኝ ተስፋ ይሆናል::

ተስፋ የሚፈልቀው ከጥበብ ዓውድ ነው:: የጥበብ ዓውደ ምህረቱ ደግሞ ተስፋ ነው:: የተስፋ ፀጋ ስጦታ ደግሞ የጥበብ ፈጣሪ መድኀኒዓለም ነው:: ተስፋችን አምላካችን፣ ዕምነታችን ነው:: ይህን በልባችን ይዘን ተስፋን በአምዳችን ሁልጊዜ እናዘምራለን::

### 8.1 ስንኘ ተስፋ አቦል መክፈቻ፣

አንደኛ:-

ተስፋ ------------ፀጋ

ተስፋ ----------- መንፈስ

ተስፋ ------------ መድህን ነው

#### 8.1.1 ስለምን ?

- ተስፋ ፀጋ ነው:- የድህረ ገፅአችን ስያሜው ፀጋዬ ስለሆነ፣
- ትልቁ የሰው ልጅ ፀጋ ተስፋ በመሆኑ፣
- በተሰጠን ፀጋ በአግባቡ በጊዜያች መጠቀም ስለአለብን፣
- ፀጋዬን መክሊታችን ነው:: መክሊታችን ደግሞ መዝራት፣ ማብቀል፣ ማምረት ትዉልዳዊ ግዴታችን በመሆኑ፣

#### 8.1.2 ተስፋ መንፈስ ነው::

ሰሙ:- ጥበብ ልዩ የሆነ ቅዱስ መንፈስ ነው::
ህሊናን ወደ ታሰበው አቅጣጫ የሚገራ

ወርቁ:- አባቶቻችን ድርሳናቸውን፣ ገድላቸውን በቅዱስ መንፈስ ተመርተው ነውና የሚከውኑት የጥበብ ታዳሚ ደግሞ ሁልጊዜ መንፈሱ ከጥበብ ጋር ወይንም ከጥበበኞች ጋር ይቆራኛል።በሞት ቢለዩ እንኳ የመንፈስ ድልድይ አለ የሚል ዕድምታ ስላለን:: በሌላ በኩል ደግሞ ሁልጊዜ ድህረ ገፅአችን ከብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ መንፈስ ጋር ይቆራኛል የሚል ራዕይም አለን::

### 8.1.3 <u>ተስፋ መድኀን ነው</u>::

ሰሙ:- የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን ምድራዊ አባቱ አቶ ገ/መድኅን
በመሆናቸው፣

ወርቁ:-

- የሎሬት መንፈሳዊ አባት መድኀኒዓለም በመሆኑ፣
  የኢትዮጵያ ፍተሀት ትንሳኤ ከእርሱ ከመድኀኒዓለም ብቻ በመሆኑ፣
- የጥበቡ ፈጣሪ መድኀኒዓለምም ጥበበኛ በመሆኑ፣

*ሁልጊዜ ሥራችን ደማችን ከሆነው ከዕምነታችን ቀኖና ዶግማ እንዲሁም
ትውፊት ጋር የተያያዘ ነው የሚሆነው::

## 9. <u>የድኅረ ገጽ መምሪያዎች</u>:-

ድኅረ ገፅ እርስ በእርሳቸው ሊዋሀዱ፣ ሊደጋገፉ፣ሊተቃቀፉ፣ ወይንም እጅ
ለእጅ ሊያያዙ የሚችሉ አምስት መምሪያዎች ይኖሩታል::
እነርሱም:-

9.1 ቃና
9.2 ማዕዶት
9.3 አብረንታንት
9.4 የሎሬት ተስፋ
9.5 ዕድምታ
እንዲሁም ትንሿ አምድ <u>መክሊት</u>

ምን ምን ሊካተቱ ይችላሉ ሲባል፣

## <u>ቃና</u>:-

ሀ. ርዕሰ አንቀጽ
ለ. መጣጥፍ
ሐ. ሀተታ
መ. ዜና
ሠ. መክሊት

## <u>ማዕዶት</u>:-

ሀ. ግጥም
ለ. ልብ ወለድ
ሐ. ስነ ቃል - ምስላዊ አባባል፣
እንቆቅልሽ፣
እንካ ሥላንቲያ ( ሊያስተምር የሚችል )
መ. ሚስጢራዊ ቅኝት

## <u>አብረንታንት</u>:-

ሀ. የወጣቶች
ለ. የሴቶች
ሐ. ማህበራዊ ኑሮ

መ. ቃለ ምልልስ
ሠ. የታዳሚ ፅሑፎች - አስተያየት
ረ. መጠነኛ የምክር አገልግሎት ለልጆች

## የሎሬት ተስፋ፣

ሀ. ልጆች / ትምህርተ ዜግነት /
ለ. ለወላጆች / መጠነኛ የምክር አገልግሎት /

## ዕድምታ:-

የኢትዮጵያ

ሀ. ታሪኳ
ለ. ባህል ( ወጓ፣ ልማዷ፣ ትውፊቷ )
ሐ. የዕውቅ ልጆቿ ታሪክ
መ. ጥንታዊና ጥናታዊ ሥራ
ሠ. የተፈጥሮ ሀብቷ
ረ. ተስፋ

የመጨረሻው የዕድምታ መምሪያ በረዥም ጊዜ መረሐ ግብራችን ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን ከሀገርም ሆነ ከሌሎች ሀገሮች ተመክሮዎች በሰፊው የሚያስፈልገው እና ጊዜን በውል የሚጠይቅ ይሆናል::

## 10. ቋንቋ:-

የድህረ ገፅ የተግባር ቋንቋ አማርኛ ሲሆን አልፎ አልፎ በጀርመንኛ፣ በእንግሊዘኛም ፅሑፎችን ለመቃኘት ይሞከራል::

## 11. የዝግጅት ክፍል፣

ዋና አዘጋጅ .......................... ሥርጉተ ሥላሴ
ኮምፒውተር ዲዛይነር ........................ ስማ በለው
የልጆች አምድ አንባቢ .......... ..................... ታዳጊ ወጣት መክሊት ከአብ

## ማጠቃለያ :-

የፈጠረን አምላክ ልዑል እግዚአብሔር እሱ በሰጠን ፀጋ በቸረን ኃይል ሥራውን ከአሰብንበት ዕለት ጀምሮ ባርኮልን፣ ፍሬማ፣ ውጤት ተደማጭነትና አክብሮት ያለው ተወዳጅ ድህረ ገፅ ያደርግልን ዘንድ ሁሌጊዜ ስንጀምር በፀሎት ስንፈፅም ደግሞ በምስጋና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የድህረ ገፅ የዝግጅት ክፍል እንድንገናኝ በፀሎት እንተሳሰባለን:: አሜን ::

ግንቦት 2000 ዓ. ም.